# በቃ - ጋዮ

ክብራትና ክቡራን ከሁሉ አስቀድሜ በዚህ መድረክ ላይ ተገኝቼ እንድናገር ስለጋበዛችሁኝ ከልብ አመሰግናለሁ። ያለንበት ወቅት የአብዮት ወቅት ነውና ለምናገር የምፈልገው በዚሁ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ነው። የዛሬው ንግግሬ ፌብርዋሪ 12 እና 13 በዳላስና ሂውስተን ያቀረብኩት አጭር ንግግር ቅጣይ ነው። በዚያ ንግግሬ ከሰሜን አፍሪቃና መካከለኛው ምሥራቅ አብዮቶች ልንማራቸው ስለሚገቡ ሶስት ነገሮችን አንስቼ ነበር። በዚያ ንግግሬ ያነሳኋቸው ነጥቦች በአጭሩ የሚከተሉት ነበሩ።

1. የነፃነትና የዲሞክራሲ ፍላጎት ለተወሰኑ ዘሮች፣ ባህሎችና ሃይማኖቶች የተሰጡ ሳይሆኑ የሰው ልጆች ሁሉ የሚፈልጓቸው እሴቶች መሆናቸውን የሰሜን አፍሪቃ አብዮቶች አሳይተውናል። "ነፃነትና ዲሞክራሲ ከምዕራባዊያን ባህልና ሃይማኖቶች ውጭ ያሉ ህዝቦች ጥያቄዎች አይደሉም" ሲሉ የነበሩ ሰዎች አሁን በሰሜን አፍሪቃና መካከለኛው ምስራቅ በሚያዩዓቸው ድንቅ ነገሮች ምክንያት እንደገና ሃሳቸውን ለመመርመር ተገደዋል።
2. የሰሜን አፍሪቃ አብዮቶች አፍሪቃዊያን በራሳቸው ያላቸውን መተማመን በከፍተኛ ደረጃ ያዳበሩት ክስተት ሆኗል። ይህ ወቅት አፍሪቃዊያን ጀግነው በምዕራባዊያን "እሹሩሩ" ሲባሉ የነበሩ አንባገነኖችን ፊት ለፊት የተጋፈጡበት አጋጣሚ ነው። ይህ ወቅት አፍሪቃዊያን "አዎ! እኛም ማድረግ እንችላለን!" Yes, We can!!! ያሉበት እና የአቅመ ቢስነት ስሜትን የረቱበት ወቅት ነው።
3. ይህ ወቅት አፍሪቃዉያን የአገራቸውና የገዛ ህይወታቸው ባለቤት የሆኑበት ወቅት ነው። ይህ ክስተት አፍሪቃዊያን የራሳቸውን እድል እራሳቸው ለመወሰን በቆራጥነት የተነሱበት አጋጣሚ ነው። በቱኒዚያና በግብጽ፤ አሁን ደግሞ በየመንና ሊቢያ ዜጎች የተደራጀና ግዙፍ ከሚመስል ኃይል "ነፃነት ወይም ሞት" ብለው ፊት ለፊት ተጋፍጠዋል:: ወጣቶች የተቃዉሞ ሰልፎችን ለመጥራት እና ራሳቸውን በግንባር ቀደምትነት ለማሰለፍ ከማንም ፈቃድ ይሁን እርዳታ አልጠበቁም። አፍሪቃዉያን የራሳቸው ባለቤት ራሳቸው የሆኑበት አጋጣሚ ነው።

በቆየንና ባሰላሰልን መጠን አዳዲስ ነጥቦችን ማግኘታችን አይቀርም። ዛሬ ከዚህ አብዮት ልንማረው የሚገባ አራተኛ ነጥብ መጨመር እንችላለን። ይህም **የአምባገነኖችን ባህርይን** የሚመለከት ነው። ይህ አብዮት ስለአምባገነኖች ባህርይ የነበረንን እውቀት በእጅጉ አዳብሮልናል ብዬ አምናለሁ።

ስለሆነም የዛሬ ንግግሬ የሚያተኩረው የአምባገነኖችን ባህርይ በተመለከተ ከሰሜን አፍሪቃና መካከለኛው ምሥራቅ አብዮቶች ልንማራቸው የሚገቡ ቁም-ነገሮች በተመለከተ ይሆናል። ስለ አምባገኖቹ ባህርይ ጥቂት ነገሮችን ከተናገርኩ በኋላ ይህ አብዮት በዓለም ዓቀፉ ማኀበረሰብ ግንዛቤ ላይ ስላመጣቸው ለውጦች ጥቂት ተጨማሪ ነገሮችን አክላለሁ። በመጨረሻም አሁን እኛ ምን ማድረግ እንደሚኖርብን ለውይይት ይጠቅሙ ይሆናል ብዬ የማምንባቸውን ነጥቦች አንስቼ ንግግሬን አጠቃልላለሁ።

## የአምባገነኖች ባህርያት

አምባገነኖች በጣም የሚመሳሰሉባቸው ብዙ ነገሮች ያሉትን ያክል አንድ ዓይነት እንዳልሆኑ ድሮም ይታወቃል። ይሁን እንጂ በአብዛኛው "በጎ አሳቢ" እና "ክፉ" አምባገነኖች ተብለው በሁለት ተከፍለው ሲጠኑ ቆይተዋል። አሁን ግን ክፉ አሳቢ አምባገነኖች ራሳቸው በብዙ ንዑሳን ክፍሎች እንደሚመደቡ አይተናል። ለተመሳሳይ የህዝብ ጥያቄ የተለያዩ ክፉ አምባገነኖች የሚሰጡት ምላሽ በእጅጉ የተለያየ እንደሆነ ቱኒዚያ፣ ግብጽ፣ የመን እና ሊቢያ ምስክሮች ናቸው።

## ቱኒዝያ

ቤን ዓሊ ከ1987 ጀምሮ በቱኒዝያ መንግሥትና ህዝብ ላይ ፈላጭ ቆራጭ የነበረ አምባገነን ነው። የቤን ዓሊና የሚስቱ አስገራሚ የሙስና ታሪኮች ገና ተጋልጠው አላለቁም። ቱኒዚያዊያን የቤን ዓሊን ሚስት ከፊሊፒንሷ ኤሜልዳ ማርቆስ ጋር ያመሷሰሏት ያለበቂ ምክንያት እንዳልሆነ ዓለም በአግራሞት እያየ ነው። በየእለቱ ማለት በሚቻል ሁኔታ ቱኒዝያ ውስጥ ተደብቆ የቆየ የሙስና ታሪክ ይጋለጣል። ከጥቂት ቀናት በፊት የቤን ዓሊ መኖሪያ ቤት ሲፈተሽ ከ10 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር በላይ የሆነ ጥሬ ገንዘብ በቁም ሣጥኖች ውስጥ ተከምሮ ተገኝቷል። እስቲ ይኼን ምን ይሉታል። የአገሪቱ ፕሬዚዳንት ያላመነውን ባንክ እንዴት ሌላ ሰው ሊያምነው ይችላል? የቢን ዓሊ የመጨረሻ ፕሬዚዳንታዊ ትዕዛዝ የሃገሪቱ ባንክ ገዢ 150 ኪግ ወርቅ ለሚስቱ ለይላ እንዲሰጥ የሰጠው ትዕዛዝ መሆኑ በራሱ የሚናገረው ብዙ ነገር አለ። ከፍቅረ-ንዋይም ባሻገር ቤን ዓሊ በሰብዓዊ መብቶች ጥሰት እና በስልጣን መባለግ ይታወቃል። ባጭሩ የቱኒዝያው ቤን ዓሊ መጥፎ አምባገነን ነበር። ያም

ሆኖ ግን ህዝቡ እንዳመረረበት ሲያውቅ በ89.62% ድምጽ በምርጫ ማሸነፉ ካስነገረ ሁለት ዓመት እንኳን ሳይሞላው ራሱ በጊዜ አገር ለቆ ወጣ።

እርግጥ ነው ህዝቡም ወታደሩም እንደከዳው ሲያውቅ ከመሸሽ የተሻለው ስላልነበረው ነው ሊባል ይችል ይሆናል። ይህንን በጊዜ ማወቅ ራሱ ትልቅ ነገር ነው። "አገርንና ህዝብን አጥፍቶ መጥፋትን" እንደ ጀግንነት የሚያዩ አምባገነኖች መኖራቸውን ስናይ ቤን ዓሊን እንድናደንቅ ያደርገናል። ቤን ዓሊ የተጨነቀው ስለራሱ ኑሮ እንጂ ለሥልጣኑ አይመስልም። ሥልጣኑንም የሚፈልገው ለተመቻቸ ኑሮ ነበር። ይበልጥ ይመቸኝ ይሆናል ወዳለው አገር በጊዜ በመሸሹ የብዙ ሰዎች ህይወት ድኗል።

**ግብጽ**

ሆስኒ ሙባረክ ከቤን ዓሊ የባሰ አምባገነን ነበር። ለሙባረክ ስልጣን የንዋይ ምንጭ ብቻ ሳይሆን የግል ክብሩ መለኪያ ነበር። የገዛ ራሱን እጅግ አግዝፎ ያይ የነበረ በመሆኑ "ሥልጣኔን አሁኑኑ ከለቀቅሁ ግብጽ የእርስ በርስ ጦርነት ውስጥ ትገባለች" ይል የነበረው የምሩን የሚያምንበትን ሊሆን ይችላል። በዚህም ምክንያት ለግል ክብሩና ለግብጽ ደህንነት ሲል ላለመውረድ የቻለውን ያህል ተግደረደረ። ይህ መግደርደር ግን ለበርካታ ህይወትና ንብረት መውደም ምክንያት ሆነ። ሙባረክን ከመውረድ ግን አላዳነውም። እንዲያውም ቅሌቱ የሙባረክ ከቤን ዓሊ ባሰ። ለሙባረክ ሥልጣንና ህይወት እኩል ሆነዋል። ያለ ፕሬዚዳንትነት ስልጣን ሙባረክ ሙባረክ አይደለም። በአሁኑ ወቅት ሙባረክ ራሱን እንደሞተ ሰው ይቆጥር ይሆናል ብዬ እገምታለሁ።

**የመን**

ዓሊ ዓብደላ ሳልህ በአፉ የሚናገረው ሌላ ቢሆንም በልቡ ራሱን የሰሜን የመን ብቻ ፕሬዚዳንት አድርጎ ይመለከት እንደነበር ሥራዎቹ ያሳብቁበታል። እንዲያውም ከዚያም በታች ወርዶ ራሱን የአንድ ጎሳ ተጠሪ አድርጎ ራሱ ወደ ማየት ራሱን አውርዷል። የመናዊያን ለሲቪል መብቶቻቸው ሲሰለፉ የእሱ ፈጣን ምላሽ የሰሜንና የደቡብ የመን ቅራኔ ነፀብራቅ አድርጎ ማቅረብ ነበር። ያ አልሳካ ሲለው ወደ ጎሳዎች ቅራኔ አወረደው። ዓሊ ዓብዳላ ሳልህ በየሰላማዊ ሰልፉ በጎሳ ፓለቲካ ምክንያት እጎኑ የቆሙትን ደጋፊዎቹን እያበረታታ ወደ ጎዳና እንዲወጡ እያደረገ በሲቪሎች መካከል የእርስ በርስ እልቂት እንዲፈጠር በብርቱ እየጣር ያለ እኩይ አምባገነን ነው። የዓሊ ዓብዳላ ሳልህ እኩይነት ትግሉ የሚያስከፍለውን ዋጋ ያበዛዋል። የሱ አወዳደቅ ግን ከሙባረክም የባሰ እንደሚሆን መገመት ይቻላል።

**ሊቢያ**

ሙዓመር ጋዳፊ የወከለው የአምባገነንነት ዓይነት ደግሞ ከሁሉም የከፋው ሳይሆን አይቀርም። ለጋዳፊ የሊቢያ ዜግነት ማረጋገጫው ጋዳፊን መውደድ ነው።
ጋዳፊ "የሊቢያ ህዝብ ሁሉ እኔን ይወደኛል፤ ለኔ ሲል ህይወቱን ይሰዋል" ሲል ደጋግሞ ተናግሯል። ለሱ ያላቸው ፍቅር የተጓደለባቸውን ሁሉ

ከሰውነት ደረጃ አውርዶ ዓይጥ፣ ቱሃንና ተባይ ናቸው ብሏል። ከአንድ ርዕሰ ብሄር እንዲህ ዓይነት ቃላት መስማት ብቻውን ይዘገንናል። "ቤት ለቤት እየሄዳችሁ እነዚህን ተባዮች ግደሏቸው" ብሎ ሲያዝ መስማት ያሸማቅቃል። ጋዳፊ በአደባባይ የሰጠው ፍርድም "በአረንጓዴው መጽሃፍ" ላይ አስቀድሞ የተፃፈ፤ በዚህም ምክንያት ትክክለኛ ፍርድ መሆኑን በቴሌቪዥን ተናግሯል።

የአምባገነኖችን ድንብርብሩ የወጣ አካሄድ (Disillusionment) ከጋዳፊ የተሻለ ገላጭ በአሁኑ ሰዓት የሚገኝ አይመስለኝም። አምባገነኖች በመደናበር የሚወስዱት እርምጃ የቱን ያህል አውዳሚ ሊሆን እንደሚችል ከጋዳፊ እንማራለን። ጋዳፊ እና ልጆቹ ስልጣናቸውን ከሚያጡ የሊቢያ ሰው በሙሉ አልቆ ምድረበዳውን ቢገዙ ይመርጣሉ። በዚህም ምክንያት ነው ቅጥረኞችን እየገዙ ዜጎቻቸውን የሚያስገድሉት።

እንዲህም ሆኖ በሊቢያ ትግሉ ቀጥሏል። ከወራት በፊት ፈጽሞ ሊገመት በማይችል ሁኔታ ዛሬ በሊቢያ ውስጥ የተጠናከረ፤ የታጠቀ ነፃ አውጭ ኃይል አለ። ይህ ነፃ አውጭ ኃይል ሊቢያን ከጋዳፊ መዳፍ መንጭቆ እንደሚያወጣት ጥርጥር የለኝም።

ያኔ የጋዳፊ መጨረሻ ምን ይሆናል? የጋዳፊና ልጆቹ መጨረሻ እስካሁን ካየናቸው ሁሉ የከፋ እንደሚሆን መገመት ይቻላል። የጋዳፊ መጨረሻ ደግሞ እየተቃረበ ነው።

**የዓለም ዓቀፉ ማኅበረሰብ**

የሰሜን አፍሪቃው አብዮት መላውን ዓለም ቀይሯል። ምዕራባዊያን ሰሜን አፍሪቃና መካከለኛውን ምሥራቅ በሚመለከት ለሠላሳ ዓመታት ሲያራምዱት የነበረው የውጭ ጉዳይ ፓሊሲ በድንገት በአፍ ጢሙ ተደፍቶባቸዋል። እስካሁን በነበራቸው የውጭ ፓሊሲ ዋነኛው ተፈላጊ ነገር መረጋጋትና የነዳጅ ስርጭቱ መሳለጥ ነበር። አሁን ግን የሰብዓዊ መብቶች አያያዝን፣ ነፃ የዲሞክራሲ ተቋማት መኖርና የመሳሰሉ መመዘኛዎች ማስገባት ሊኖርባቸው ነው። ይህ በፓሊሲ እንዴት እንደሚገለጽ ለማውጠንጠን እንኳ ፋታ አላገኙም። በዚህም ምክንያት እነሱም ድንብርብራቸው ወጥቷል።

የሆነ ሆኖ  አሁን ባለው ሁኔታ ከነፃነት ናፋቂው ህዝብ ጎን መቆም ግዴታ ሆኖባቸዋል። በተለይ የጋዳፊ ክፋት ቻይናና ሩሲያ እንኳን ሳይቀሩ ጣቶቻቸውን እንዲቀስሩባቸው አድርጓቸዋል።

የዓለም ዓቀፍ ፍርድ ቤት በጋዳፊ፣ በልጆቹና ተባባሪዎቹ ላይ ደግሞ ክስ ሊመሰርት ዝግጅቱ አጠናቋል። ዓለም በአምባገነኖች ላይ እንዲህ በጋራ አድሞ አያውቅም። የተባበሩት መንግሥታት የፀጥታው ም/ቤት ጋዳፊ፣ ልጆቹና ተባባሪዎቻቸው እንዲከሰሱ ማዘዙ እና አሁን ደግሞ  የአማጺያኑን መንግሥት የተባበሩት መንግሥታት እውቅና እንዲሰጠው እየተደረገ ያለው ጥረት እጅግ አበረታች ነገር ነው። አምባገነኖች እስከ ጠቀሟት ድረስ ክፉ ነገር ተናግራ የማታውቀው ፈረንሳይ እንኳን የሊቢያን አማጽያን በመንግስትነት ማወቋ ዓለም እንዴት እየተቀየረች እንደሆነ በመጠኑም ቢሆን አመልካች ነው።

ከመንግሥታትም ባለፈ አብዮቱ በዓለም ህዝብ ላይ ያሳደረው ስነ-ልቦናዊ ተጽዕኖ  ቀላል አይደለም። የምዕራቡ አገራት ታዋቂ ሰዎችና ባለሥልጣኖች ከአምባገነኖች ጋር የነበራቸው ግኑኝነት ለቅሌት ዳርጓቸዋል። አንዳንዶች በዚህ ምክንያት ሥራ እየለቀቁ፤ ሌሎች ደግሞ ከአምባገነኖች ጋር ተሞዳሙደው ያገኙትን ገንዘብ ለበጎ አድራጎት ድርጅቶች እንዲያስረክቡ እየተደረገ  ነው።

ቅሌቱ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትንም ነካክቷል። London School of Economics ከጋዳፊ ፈንድ 1.5 ሚሊዮን ፓውንድ በእርዳታ በመቀበሉ ተማሪዎች ባስነሱት አድማ ምክንያት የትምህርት ቤቱ ዳይሬክተርና የጋዳፊ ፈንድ የቦርድ አባል የነበሩት የኖቤል ሽልማት ተሸላሚው ሰር ሃዋርድ ዴቪስ በቅሌት ሥልጣናቸውን ለቀዋል። ሌሎች ሁለት ዩኒቨርስቲዎችም[1] ተቃውሞ በርክቶባቸዋል። ይህ ደግሞ  ይቀጥላል። በኋላ የምመለስበት ቢሆንም በዚህ ረገድ እኛም ልናጋልጣቸው የሚገቡ በርካታ “ምሁር ነን ባይ” ታዋቂ ሰዎችና ተቋማት እንዳሉ ማስታወስ እፈልጋለሁ።

አብዮቱ አድማሱ እያሰፋ ነው የሚለው ግምት እያደር እየጠነከረ ነው። በተለይ የቻይና ኮሚኒስት-ከበርቴ-አምባገነኖች በዚህ አብዮት ተረብሸዋል። አብዮቱ ከተነሳ ማስቆም እንደማይቻል አይተዋልና መላውን ኃይላቸው እንዳይነሳ በማድረግ ላይ አውለውታል። ይህ ደግሞ ሌላ ችግር ጎትቶ  ሊያመጣባቸው ይችላል።

የደቡብ ኮሪያ ወጣቶች የታህሪር አደባባይ ፎቶዎችን በፊኛዎች አስረው ለሰሜን ኮሪያዎች ዜጎች ልከውላቸዋል።  ከሰሃራ በታች ባሉ አፍሪቃ አገራት ውስጥ ደግሞ አብዮት የዘወትር መነጋገሪያም ማስፈራሪያ ሆኗል። በምርጫ እንወዳደራለን የሚሉት እንኳን ሳይቀሩ “ታጭበረብርና ዋ!!! የግብጹን ዓይነት አብዮት አስነሳብሃለሁ” እያሉ ማስፈራራት ጀምረዋል።
ባጭሩ ዓለም ለአምባገነኖች የነበረው ትዕግሥት አልቆ እንጥፍጣፊው ብቻ ነው የቀረው።

**ምን እናድርግ?**

ትልቁ ጥያቄ “ይህ አብዮት አገራችን እንዲደርስ እና ውጤታማም እንዲሆን ምን እናድርግ?”  የሚለው ነው። ማድረግ የሚገቡን ጉዳዮችን በሶስት ዋና ዋና ክፍሎች መክፈል ይቻላል ብዬ አምናለሁ። እነሱም 1ኛ) ጠላትን መነጠል፣ 2ኛ) ወዳጅ ማብዛት፣ እና 3ኛ) ጥቃት መጀመር ብዬ ሰይሜዓቸዋለሁ።

---

[1] . *ሁለቱ ተጨማሪ ተቋማት* The School of Oriental and African Studies እና King’s College in London

## 1. ጠላትን መነጠል

ጠላትን መነጠል ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ተግባር ነው። በግንቦት 7 ንቅናቄ ውስጥ ያለን ሰዎች ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ወያኔ የሚለው አጠራር ትተን "የትግራይ ገዢ ጉጅሌ" የምንለው ያለ ምክንያት አይደለም። "ጉጅሌ" የትግርኛ ቃል ሲሆን ትርጉሙም "ቡድን" ማለት ነው። በእኛ እምነት አሁን የመለስ ቡድን ድሮ ከምናውቀው "ወያኔ" በታች ዘቅጦ የጥቂት ማፍያ ግለሰቦች ስብስብ ሆኗል። ይህ የማፍያ ስብስብ የተዋቀረው በመለስ ዜናዊ፣ ስብሃት ነጋ፣ ስዩም መስፍን፣ በረከት ስምኦን፣ አዜብ መስፍን፣ አባይ ፀሃዬ፣ ሳሞራ የኑስ እና ጥቂት ተጨማሪ የትግራይ ተወላጆች ነው። ይህንን ቡድን ከትግራይ ህዝብ ብቻ ሳይሆን ከወያኔ አባላትም ጭምር ነጥለን ለማውጣት "የትግራይ ገዢ ጉጅሌ" የሚለውን አጠራር መጠቀም መርጠናል።

ይህ የገዢዎች ቡድን በየክልሉ ባስቀመጣቸው ምስለኔዎች አማካይነት መላዋን ኢትዮጵያን እየገዛ ነው። ይህ ቡድን ሥልጣኑን ከሚያጣ ትግራይን ሳይቀር ከማጋየት የማይመለስ እኩይ ኃይል ነው። የትግራይ ገዢ ጉጅሌ የትግራይን ሰፊ ህዝብ ጨምሮ የኢትዮጵያዊያን ሁሉ ጠላት እንደሆነ ማመንና ማሳመን ይኖርብናል። ይህን የምናደርገው ደግሞ እኛ ራሳችን በተግባር በጋራ ስንቆም ነው።

የነፃነት ትግል ህዝብን ያፋቅራል። ይህንን አብዮት በተካሄደባቸው የሰሜን አፍሪቃ አገሮች ሁሉ አይተነዋል። እኛም አገር የፀረ የትግራይ ገዢ ጉጅሌ ትግል ኢትዮጵያዊያንን እንደሚያፋቅር በተግባር ማሳየት ይኖርብናል።
ስለዚህም በንግግሮቻችንና በጽሁፎቻችን ሁሉ ጠላታችን የትግራይ ገዢ ጉጅሌ **ብቻ** መሆኑ፤ ይህ ጉጅሌ ደግሞ ትንሽ የማፍያ ቡድን እንደሆነ ማስረገጥ ይኖርብናል።

## 2. ወዳጅ ማብዛት

የአብዮቱ ወገኖችን ባበዛን መጠን ገዢውን ጉጅሌ እያደከምን እንሄዳለን። አሁን ገዢው ጉጅሌ የራሱ ያደረጋቸው የሚመስለውን ኢትዮጵያዊያን ተቋማትን ወደ ራሳችን ማምጣት ቅድሚያ ተሰጥቶት ሊሰራበት የሚገባ ጉዳይ ነው። በተለይም የሚከተሉት ነጥቦች ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል።

- የኢትዮጵያ የመከላከያ ሠራዊት የኢትዮጵያ አለኝታ መሆኑ እንዲሰማው ማድረግ ያለብን አሁን ነው። ጥርጣሬዓችን ያለው በአመራሩ ላይ እንጂ በሠራዊቱ ላይ አይደለም። በመከላከያ ሠራዊት ውስጥ በሚገኙ የበታች አለቆችና ወታደሮች ላይ እየደረሰ ያለው የሙብት ረገጣ ዘግናኝ መሆኑን እናውቃለን። ህልማችን ህልማቸው ስለ መሆኑ ጥርጣሬ የለንም። የቁርጥ ቀን ሲመጣ ሠራዊቱ የራሱን አመራር የሚያመጣበት መንገድ አለ ብዬ አምናለሁ። ሆኖም ግን ሠራዊቱ ለዚህ እንዲዘጋጅ በውስጡ ያሉ ወዳጆቻችንን፣ ዘመዶቻችንና ጓደኞቻችንን በድፍረት ልናነጋግራቸው ይገባል።
- ኢህአዴግ የሚባለው ድርጅት በመሠረቱ አለ ለማለት አያስደፍርም። የኢህአዴግ አባል ድርጅቶቹ መሪዎች በህዋህት በሚደረግባቸው ወከባ ልባቸው እየደማ መሆኑን እናውቃለን። እነዚህ ድርጅቶች ራሳቸውን ነፃ እንዲያወጡ መንገድ ሊመቻችላቸው ይገባል።
- አሁን ያለው ህዋህት የድሮዉ ህዋህት አይደለም። ብዙዎች ህይወታቸውን የሰውለት ድርጅት ዛሬ የጥቂቶች ኑሮ ማሞቂያ ሆኗል። የድሮዉ ወያኔ ፍቅር ያላችሁ ወገኖች ከዛሬዎች ወራዳዎች እራሳችውን እንዲያርቁ ልንረዳቸው ይገባል።

## 3. ጥቃት መጀመር

በአገር ቤት ውስጥ መደረግ ስለሚኖርበት ጥቃት በዚህ መድረክ ላይ መናገር እንደሌለብኝ ትረዱልኛላችሁ ብዬ አምናለሁ። ሆኖም በውጭ አገራት ውስጥ መጀመር ስለሚኖርበት የማጥቃት እርምጃ መናገር እፈልጋለሁ። አዎ!!!! እስከዛሬ ወያኔ አጀንዳ እየፈጠረልን እኛ እሱ ላይ ስንራኮት ቆይተናል። አሁን ጨዋታው ተቀይሯል። ዛሬ አጥቂዎቹ እኛ ነን። የጥቃት ዘመቻችን ዛሬውኑ መጀመር ይኖርብናል። የማጥቃቱ እርምጃ ባለብዙ ዘርፍ መሆን ይኖርበታል፤ ለምሳሌ:-

- በብዙ አቅጣጫዎች የሚዲያ ጥቃት መካሄድ አለበት። ኢሳት ወያኔን ወደ ተከላካይነት አውርዶታል። ኢሳትን በመደገፍ በብዙ ፍሪኩዌንሲዎች አገር ቤት እንዲገባ ማገዝ ይኖርብናል። ከዚህም በተጨማሪ የአጭር ሞገድ ሬድዮኖች ዝግጅቶቻቸውን ማቀናጀት ይገባቸዋል። እንደ Facebook እና Twitter ዓይነት ማዕበራዊ የኤሌክሮኒክስ ሚዲያዎች ኢትዮጵያዊን ለመድረስ እንጠቀምባቸው።
- በአውሮፓና ሰሜን አሜሪካ የሚገኙ ሊቢያዊያን ከጋዳፊ ጋር ሲሞዳሞዱ የነበሩትን ምዕራባዊያን መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማትን እና ታዋቂ ግለሰቦችን በማጋለጥና በማሳፈር የሚደነቁ ተግባራትን ሰርተዋል። በውጭ አገራት የምንገኝ ኢትዮጵያዊያን ተመሳሳይ ነገሮችን በመስራት ጥቃት መጀመር አለብን። ለምሳሌ ለወያኔ ባለሥልጣናት ዲግሬ ሲያድሉ የቆዩ የትምህርት ተቋማት እነማን ናቸው? እነዚህ ተቋማት በአገራቸው ህዝብና ሚዲያ ማሳፈር ትልቅ ዋጋ ያለው ተግባር ነው። ለመለስ ዜናዊ የተውገረገረ የኢኮኖሚ ፓሊሲ ጥብቆ ቆመው እየተከራከሩ ያሉ ታዋቂ ሰዎችንም ጭምር በ London School of Economics እና በፕሮፌሰር ሃዋርድ ዴቪስ የደረሰውን ማስታወስ እና ይህንን ለአገር ዜና ማብቃት የማጥቃት እርምጃ ነው።
- በለንደን የሚገኙ ሊቢያዊያን የጋዳፊ ልጅ የሰይፍ አልኢስላም ቪላን በጉልበት መያዛቸው ለእኛም ትምህርት ሊሰጠን ይገባል ብዬ አምናለሁ። የትግራዩ ገዢ ጉጅሌ አባላት ምን ያህል ንብረት በአውሮፓና አሜሪካ አደራጅተዋል፤ ምን ያህል ቤት ሠርተዋል? ለልጆቻቸው ትምህርት ምንያህል ይከፍላሉ? ይህንና የመሳለውን አደባባይ ማውጣት የማጥቃት እርምጃ ነው።

አገር ቤት ያሉ ወጣቶችን "በዚህ ቀን ተነሱ" ከምንል እኛ አጠገባችን ባለው ጠላትና የጠላት ወዳጅ ላይ ብናምጽ የተሻለ ጥቅም እንሰጣለን። አገር ቤት ያሉ ወጣቶች እኛን አይተው ይበረታታሉ።

ከሁሉም በላይ ደግሞ በአገር ቤት የሚደረገው አመፃ የሚዲያ ሽፋንና ትኩረት እንዲያገኝ ማድረግ የሚችለው በውጭ አገራት የምንገኘው ነኝ። በቂ የሚድያ ሽፋን መስጠት ብንችል ኖሮ ሰሞኑት በጋሞ ጎፋና በአዋሳ የነበሩ መነሳሳቶች አገር አቀፍ ህዝባዊ አመጽ ለመቀስቀስ ከበቂ በላይ ክብሪቶች ናቸው። ይህም ሆኖ ግን አገር ውስጥ ላለው ማህበረሰብ የምንሰጠው መልእክት ተመሳሳይ መሆን አለበት:: ሁሉም የራሱን ጥሪ በየግሉ ከማድረግ፤ የአገሩንና የውጭውን እንቅስቃሴ የማቀናበሩን ስራ በአስቸኳይ መስመር ማስያዝ አለብን:: ለዚህ ደግሞ በተቃዋሚ ሀይላት መሀል የተጀመሩ የመቀራረብ ውይይቶች ቀጠሮ ሳይሰጣቸው በአስቸኩዋይ እልባት አግኝተው የጋራ ትግሉ በተባበረ ድርጅታዊ ሀይል መመራት አለበት::

**ማጠቃለያ**

በመጨረሻም በማጠቃለያ ምትክ ይህንን አጋጣሚ ተጠቅሜ አንዳንድ ማሳሰቢያዎችንና ጥሪዎችን እንዳቀርብ ይፈቀድልኝ።

**ለኢትዮጵያ ህዝብ**

*ወጣት ልጆችህ ለሃያ ዓመታት ተንሰራፍቶ የኖረን፤ ለችግርና እርዛት የዳረገህን አምባገነን ሥርዓትን ለመቃወም እና ሰብዓዊ ሙብቶቻቸውን ለማስከበር ወደ አደባባይ መውጣታቸው አይቀርም። ይህ አምባገነን ይሉኝታና አዘኔታ የማያውቅ በመሆኑ ሁላችን በጋራ መነሳት ግዴታችን ነው። ትግሉ የወጣቶች፣ የወንዶች፣ የክርስቲያኖች፣ ወይም ደግሞ የአንድ ወይም የሁለት ብሄር ተወላጆች አድርገው ሊያቀርቡት መሞከራቸው አይቀርም።፤አትስማቸው። **ትግሉ የጋራችን ነው**!!! ስለዚህም አጠገብህ ያሉ ወጣቶች በተነሱ ጊዜ አብራሃቸው ቁም። እናቶችና አባቶች ከልጆቻቸው ጎን ቁሙ!!! ዘር፣ ሃይማኖት፣ ጾታ እና እድሜ አይለዩንም። ሁላችንም በአንድነት "በቃ - ጋዬ" ማለት አለብን።*

**ለመከላከያ ሠራዊት አባላት**

*እየደረሰብህ ያለውን የሙብት ረገጣ እናውቃለን። የኢትዮጵያ ህዝብ፣ ሠራዊቱ የአብራኩ ክፋይ እንደሆነ ያውቃል። ሠራዊቱ የህዝብና የአገር መከታ እንጂ የአንድ ዘረኛ ቡድን መጠቀሚያ መሆን በጭራሽ የለበትም። ስለሆነም ከወገኖችህ ጎን ለመቆም የግል ውሳኔ አድርግ። እንዲህ ዓይነቱ ውሳኔ የወቅቱ ነፋስ ታይቶ የሚደረግ ሳይሆን የመርህ ጉዳይ ነው። በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊያን ወገኖችህ ላይ እጅህን አታንሳ። ይልቁንስ በገዛ አገራችን ባርነትን ያወጁብንን የጥቂት አምባገነኖች ቡድን ለማስወገድ በምናደርገው ትግል የበኩልህን ተሳትፎ አድርግ።*

**ለትግራዩ ገዢ ጉጅሌ አባላት**

ዘመን ተቀይሯል። እንደ ድህረ ምርጫ 97 ተቃማሚዎችን ገድሎና አስሮ አገዛዝን ማስቀጠል ይቻላል ብላችሁ አታስቡ። እኛ ኢትዮጵያዊያን ግፍ መሮናል። በቃ-ጋዮ ብለናል!!! አምርረናል!!! በዘር፣ በሃይማኖት፣ በጾታ፣ በሥራ ዓይነት ከፋፍላችሁ እያጣላችሁ እስካሁን ኖራችሁ፤ ካሁን በኋላ ግን እርማችሁን አውጡ - አንከፋፈልም!!!!

በሥልጣን ላይ በቆያችሁ መጠን አወዳደቃችሁ የከፋ እንዲሆን ታደርጉታላችሁ። ህዝባዊው አመጽ እንዴትና የት እንደሚፈነዳ ማወቅ አትችሉም። ማንም ይህንን አያውቅም። ዓለም አምባገነንነት ሰልችቶታል። ዓለም የውሸት ምርጫ ሰልችቶታል። የኢትዮጵያ ህዝብ ሰልችቶቻል። ማንገራገር ትርፉ በጋዳፊ ላይ እየደረሰው ያለውን ዓለም ዓቀፍ ውግዘት መሆኑ ልብ በሉ። ለራሳችሁና ለልጆቻችሁ ስትሉ አወዳደቃችሁን አሳምሩ።

**ለህዋህት አባላት**

ድሮ የምታውቁትና የምትወዱት ወያኔ ዛሬ የለም። እስከ መቼ የመለስ፣ የስብሃትና የአዜብ አሽከሮች ሆናችሁ ትኖራላችሁ? እውስጣችሁ ያለውን ቁጭት እንረዳለን። ጥርጣሬን ከልባችሁ አውጡና የኢትዮጵያን ህዝብ የነፃነት ትግል ተቀላቀሉ።

**ለኢህአዴግ አባላት**

የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች መሪዎች ቆም ብላችሁ ራሳችሁን የምትመረምሩበት ወቅት ደርሷል። ሰው ባርያነቱን ለማወቅ ስንት ዓመት ይፈጅበታል?

ተመልከቱ ቱኒዚያና ግብጽ ያ ሁሉ ሠራዊት፣ ያ ሁሉ ድርጅት፣ ያ ሁሉ ጆሮ ጠቢ የነበረው አገዛዝ ለመፍረስ ወራት አልፈጀም። በህዝብ ልብ ውስጥ የሌለ ሥርዓት መሠረት የሌለው ዛፍ ነው፤ ንፋስ ሽው ባለ ጊዜ ይገነደሳል።

ሊቢያን ተመልከቱ!!! የአፍሪቃ አገራት መሪዎችን ሳይቀር ያርበደብድ የነበረው ጋዳፊ ጠመንጃ ካነሱ ወር እንኳን ያልሞላቸው ሰዎች "አማጽያን" ተብለው አብዛኛው የአገሩ ክፍል ተይዞበታል። ሊቢያ ውስጥ ከጥቂት ወራት በፊት ተቃዋሚ የሚባል ኃይል አልነበረባትም። አሁን ግን ለአይሮፕላን ውጊያ ምላሽ የሚሰጥ የነፃ አውጭ ሠራዊት አለ። የትግራይ ገኘ ጉጅሌ የተደላደለና የማይነቃነቅ አይምሰላችሁ።

ለኦህዴድ፣ ለብአዴን እና ለደህዴድ መሪዎች ጥሪዬን አቀርባለሁ። ራሳችሁና ድርጅታችሁን ከገዢው የነመለስ ቡድን አግልሉ!!! እነሱ እንደሆን ከተቃዋሚዎቻቸው በላይ የሚንቁት እናንተን ነው:: ከመሳሪያነት በላይ ትንስም ክብር ለናንተ የላቸውም:: ሳይረፍድ አሁኑኑ ይህንን ካደረጋችሁ የኢትዮጵያ ህዝብ መሃሪ ነው። እናንተም ከህሊና ወቀሳ ትድናላችሁ። ስለሆነም ከትግራዩ ገዢ ጉጅሌ ርቃችሁ ከህዝብ ጎን ቁሙ።

**እኛ በቃ ብለናል!!! በቃ - ጋዮ ብለናል።**